# ለዩው ኢየሱስ

# Jesus the Separator




***(ዮሐንስ 9:39)*** *ኢየሱስም። የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ [እንደ ለዩ፥ በእኔ በሚያምኑትና እኔን ሳይቀበሉኝ በቀሩት መካከል ልዩነት(Separation) ይኖር ዘንድ] መጣሁ አለ።*

የሚያምኑትን ከማያምኑት ለመለየት ጌታ አሁን እንደ ለዪ እየመጣ ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ፍርያማዎች እንጂ እውራን እንዳይሆኑ በሕይወታቸው ውስጥ የእርሱን ራእይ ያካፍላቸው ዘንድ በእርሱ አምነው እውር እምነት ላላቸው እይታን(ብርሃንን) ለመስጠት እየመጣ ነው።

ሃይማኖተኛ(religious) ለሆኑና ሃይማኖታዊ መንፈስ(religious spirit) ያላቸው ሁሉንም አውቀነዋል ብለው ያምናሉ። ሃይማኖታዊ መንፈስ ሕጋዊ ነው፣ ግምት(በእውነት ወይም በእውቀት ላይ ያልተመሠረተ አመለካከት) ነው፣ ክርክር ነው፣ ፈራጅ እና አስጊ ነው፤ እነርሱ የእውነት እውር(የታወሩት) ናቸው። መንገዱን በአዕምሮዋቸው እንዳወቁት እያሰቡ እና በእርግጥ ምንም መልስ ሳይኖራቸው እነርሱ ግን መልሶች ሁሉ እንዳላቸው ያስባሉ። ኢየሱስ ብቸኛው መልስ ነው!

እውር እምነት ያላቸው እነዚያ እውር ናቸውና መምህሩን ይከተሉታል የእርሱን ድምፅ ግን ያውቃሉ እነርሱም ሌላ አይከተሉም። ስለዚህ እርሱ እይታ ሊሰጣቸው እየመጣ ነው። የሌሎችን ድምፅ ስለማይከተሉ በእርግጥ ከእነርሱ እንደሚሸሹ አያውቁም።

***(ዮሐንስ 10:5)*** *ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ [በምንም ሁኔታ] አይከተሉትም፥ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።*

እውር እምነት ቢኖራቸውም፥ ጌታን ይከተሉታል እርሱም በሮቹን ለእነርሱ ይከፍትላቸዋል ፍላጎታቸወንም ያማላል እነርሱም እኔን በእውር እምነት ይከተሉኛል።

**(ዮሐንስ 10:9)** *በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል (ይኖራል)፥ ይገባልም ይወጣልም [በነጻነት] መሰማሪያም ያገኛል።*

**(ዮሐንስ 10:14-15)** *መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ።*

ሁሉንም በአዕምሮዋቸው ያወቁ የእውነት እውር ናቸው እኔም ምን እያደረግሁ እንደሆነ አያውቁምም። እኔ መንፈስ ነኝና ወደ ሰው መንፈስ ውስጥ እናገራለሁም በዚያ ነው የእኔን ድምፅ እርሱ የሚሰማው። ሃይማኖታዊ ሰው ግን መንፈሳዊ ስላልሆነ ድምፄን አይሰማም፤ በእርሱ ውስጥ ያለው የእኔ መንፈስ ሳይሆን የእርሱ አዕምሮ እየተቆጣጠረ ነው። ስለዚህ በእኔ የሚያምኑትን ድምፄንም የሚሰሙትን ከሚዳፈሩት(presumptuous)፣ ራስ ተኮር(ወዳድ)(self centered) ከሆኑትና ሃይማኖታዊ(religious) ከሆኑት ለመለየት እኔ መጥቻለሁ።

## ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

ስም የሌለው፥ የማይታወቅ፥ ጌታውና አምላኩ በሆነ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸንቶ የሚኖርና የሚታመን፥ ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ አንድ የማይጠቅም ባሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ተረጎመው። ክብር ሁሉ፣ ኃይልም ብርታትና ጥበብም ውዳሴና ምስጋናም፣ ግርማና ሞገስም፣ ዝማሬና እልልታም ማዳንና ቅድስና ለቡሩክ መልካም ቅዱስ የእስራኤል አምላክ ለአባታችን ለእግዚአብሔር አብ ይሁን ለታረደው በጉም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቡሩክ ቅዱስ መንፈሱም ብቻ ይሁን አሜን ሃሌ ሉያ። ማራናታ ጌታ ያሑሹዋ ሐማሺያክ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቶሎ ና አሜን!

http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.Jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ , http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com , **http://www.bobjones.org/** , http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.bullsere.kr/ , http://www.blogtalkradio/thelordshour , http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth , http://www.be4thefire.com/ , http://www.e-sword.net/ , http://lamarzulli.net/ , http://www.blogtalkradio.com/coming-apocalypse , http://copticchurch.net/ , http://www.irisglobal.org/ ,

http://www.morningstarministries.org/